# የተማሪ ምደባ

## <u>የትምህርት መከታተል ቦታዎች</u>

ለእያንዳንዱ ት/ቤት የትምህርት የመከታተያ ቦታ በትምህርት ቤት ቦርዱ ይወስናል። ተማሪዎች የሚሄዱበት ትምህርት ቤት ትምህርት የሚከታተሉት እነርሱ በሚኖሩበት በተከለለ ወይም በተመደበ አካባቢ ዞን ይሆናል በሱፐር ኢንቴንደንቱ ወይም በተወካዮ የተለይ ልዮ ፍቃድ እስካልተሰጠ ድረስ ። ሱፐር ኢንቴንደንቱ የተማሪዎችን ምደባ ለመወሰን ልዩ ደንብ ያወጣል(ደንብ JC-R/JCD-R)።

የትምህርት ቤት ዞን ለውጥ ሃሳብ ሱፐር ኢንቴንደንቱ ለትምህርት ቤቱ ቦርድ ይቀርባል።የሚቀርበው የለውጥ ሃሳብ የሚመሰረተው ትምህርት ቤቶችን በስርዓት ለማስተዳደር ፣ብቁ የትምህርት አሰጣጥ እና የተማሪዎችን ጥበቃ፣ ጤና፣ የተሻለ ፍላጎት ማሟላት እና አጠቃላይ ደህንነት ከማስጠበቅ ካለው አመቺነት አንፃር ነው።

በቨርጅኒያ ህግ እንደተጠቀሰው የሱፐር ኢንቴንደንቱ የሚያቀርበው ሃሳብ የአንደኛ ደረጃ የተማሪዎች ቁጥር የክፍል መጠን የሚወሰነው በየዓመቱ በጸደይ (ስፐሪንግ) ወራት የበጀት ስራ በሚከናወንበት ወቅት ነው። በተመሳሳይ ወቅት ሱፐር ኢንቴንደንቱ ለእያንዳንዱ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ የሆምሩም ክፍሎችን ቁጥር ሃሳብ ያቀርባል።

## <u>የተማሪ ምደባ አማራጮች</u>

### I. የስፋት መጠን መልሶ ምደባ

የትምህርት ቤቱን ቦርድ በመወከል የሱፐር ኢንቴንደንቱ በአንድ የተወሰነ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ወይም በአንድ የክፍል ደረጃ የሚመደቡ ተማሪዎችን ቁጥር መገደብ ይችላል።የሱፐር ኢንቴንደንቱ እንደነዚህ ዓይነት ተማሪዎች ከሚኖሩበት በአቅራቢያቸው በሚገኙ የመቀበል አቅም ባላቸው ሌሎች ትምህርት ቤቶች በስርዓቱ እንደገና የሚደለደሉበትን የአሰራር ሂዳት ያዘጋጃል(ደንብ JC-R/JCD-R )። የኤሲፒኤስ የትራንስፖርት እና አጠቃቀም በምደባው አሰራር ላይ ተጽእኖ የሚኖረው በመሆኑ "ከተማሪው መኖሪያ በቅርብ ያለ ትምህርት ቤት" በአጭር የመንዳት ርቀት(በማይል) ነው የሚወሰነው ። ይህ መልሶ የመመደብ አሰራር የሚካሄደው በሚከተሉት ሁኔታዎች ነው፤

- የትምህርት ቤት ቦርዱ በትምህርት አለም ቀጣይነት እና መረጋጋት ያለውን ጠቀሜታ ይረዳል። ነገር ግን የአንድ የክፍል ደረጃ የተማሪ መጠን በሚሞላበት ወቅት በአንድ የአንደኛ ደረጃ እና የሆም ሩም ክፍሎች ቁጥር ከተወሰነው መጠን በላይ ሲሞላ ትርፍ ተማሪዎች ከሚኖሩበት በአቅራቢያቸው በሚገኙ በዚያ የክፍል ደረጃ የመቀበል አቅም ባላቸው ትምህርት ቤቶች እንደገና ይመደባሉ። በትምህርት ቤቱ የተመደበ ማንኛውም ተማሪ በአቅም ምክንያት እንደገና እንዲዛወር አይደረግም ። (ይህ ከትምህርት ቤት የቀየሩትን ልጆች እና በአስተዳደር ፈቃድ እስከ አመት መጨረሻ እንዲቆዩ የተፈቀደላቸውን ተማሪዎች አይመለከትም። እንዲሁም በዲቪዝኑ በሙሉ እንደገና ምደባ እንዲደረግ በትምህርት ቤቱ ቦርድ የጸደቀውን አይመለከትም።)

- በቀጣዩ የትምህርት ዓመት ሲጀመር ወደ መደበኛ የአካባቢያቸው ትምህርት ቤት ለመመለስ ቦታ የሚገኝ ከሆነ በቦታ መጣበብ ምክንያት በሌላ ት/ቤት የተመደቡ ተማሪዎች ስም ባላቸው ውጤት ቅደም ተከተል መሰረት በተጠባባቂ ዝርዝር መዝገብ ውስጥ እንዲቆይ ይደረጋል ።

- የክፍሉ መጠን የሞላ ቢሆንም እንኳ የትምህርት ቤቱ የወቅቱ ተማሪዎች የሆኑ ወንድምና እህት በዚያው ትምህርት ቤት እንዲመደቡ ይደረጋል ።

ኤሲፒኤስ በወታደራዊ አገልግሎት የተሰማሩ የሚያደርጉትን አስተዋፅኦ ይገነዘባል። በመሆኑም የሰራዊቱ አባላት ልጆችን የመቀበል ስራ በ [Interstate Compact on Educational Opportunity for Military Children](Interstate Compact on Educational Opportunity for Military Children) (ቨርጂኒያ ህግ [§ 22.1-360](§ 22.1-360)) በተገለፀው መሰረት ያከናውናል። ይህም የሚያካትተው ምንም እንኳ የክፍሉ መጠን የሞላ ቢሆንም ቀደም ሲል ምድባቸውን ከመቀየራቸው በፊት ሲከታተሉበት በነበረው ትምህርት ቤት መመለስ ወይም የሰራዊቱ ቤተሰብ በሚኖሩበት አካባቢ በሚገኝ ትምህርት ቤት መመደብ ይጨምራል።

- ሌላ የተማሪ አማራጭ ምደባ ከመደረጉ በፊት ሁሉም ተማሪዎች በአካባቢያቸው ባለው ትምህርት ቤት በቅድሚያ መመዝገብ አላባቸው ።

በአቅም ምክንያት ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ለተመደቡ ተማሪዎች ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ የትራንስፖርት  አገልግሎት ይሰጣል።

## II. የፕሮግራም ዝውውር

በትምህርት ቤት ፕሮግራምን መሰረት በማድረግ የእነርሱ ተማሪ በኤሲፒኤስ ውስጥ እንዲዛወር ወላጆች መጠየቅ ይችላሉ። የተመረጡ የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች ማለት የጥንድ ቋንቋ ፕሮግራም ፣ የመዋእለ ህጻናት - 8 ፕሮግራም እና የተሻሻለ ጊዜ ሰሌዳ (ካላንደር)ፕሮግራም ናቸው። እኒዚህ ፕሮግራሞች በቅድሚያ በትምህርት ቤቱ ዞን ለሚኖሩ ተማሪዎች ክፍት ናቸው። እነዚህ ትምህርት ቤቶች በተጠየቀው የክፍል ደረጃ ክፍት ቦታ የሚኖር ከሆነ ከሌላ የትምህርት ቤት ዞን ዝውውር ይቀበላሉ ። የፕሮግራም ዝውውር ጥያቄዎች የሚፀድቁት በሱፐር ኢንቴንደንት ወይም በተወካዮ ነው።

የፕሮግራም ዝውውር ተቀባይነት ካገኘ የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል።

ለተመረጠው የትምህርት ፕሮግራም ዝውውር ከተጠየቀው አመልካች ብዛት ያነሰ ቦታ የሚኖር ከሆነ የተማሪውን ምደባ ለመወሰን እጣ እንዲወጣ ይደረጋል። የሎተሪ እጣ የሚወጣው ለክፍል ደረጃ ምደባ ብቻ ነው።
እንደሌሎቹ የዝውውር አይነቶች ሁሉም ተማሪዎች የፕሮግራም ዝውውር ከመጠየቃቸው በፊት በመኖሪያ ምድባቸው ባሉ ትምህርት ቤቶች መመዝገብ አለባቸው።

የፕሮግራም ዝውውር ያገኙ ተማሪዎች በቀጣዩ የትምህርት አመት መጀመሪያ ላይ በመኖሪያ ዞናቸው ወደ አለው ትምህርት ቤት እንዲመለሱ መጠየቅ ይችላሉ። እነዚህ ጥያቄዎች ተቀባይነት የሚያገኙት በተጠየቀው የክፍል ደረጃ ክፍት ቦታ የሚኖር ከሆነ ነው። በትምህርት ዓመቱ የሚቀርቡ ማናቸውም ጥያቄዎች እንደየጥያቄው ሁኔታ አንድ በአንድ ይታያሉ።

### የጥምር ቋንቋ ፕሮግራም

የፕሮግራሙን የቅደም ተከተል ሂደትና ከትምህርት አሰጣጥ መሰፈርት ጋር ያለውን ትስስር በመመልከት ተማሪዎች የጥምር ቋንቋ ፕሮግራም መጀመር የሚገባቸው በህፃናት መዋያ ወይም አንደኛ ክፍል ነው። ማንኛውም ከክፍል 2-5 ባለ የክፍል ደረጃ በጥምር ቋንቋ ፕሮግራም ለመግባት የሚቀርብ የተማሪ ጥያቄ የተማሪውን በተገቢው በክፍል ደረጃ በፕሮግራሙ ሙሉ በሙሉ የመግባትና የመሳተፍ አቅም ለማረጋገጥ እንደየሁኔታው ይመረመራል።

በጥንድ ቋንቋ ፕሮግራም መሳተፍ የማይፈልጉ ተማሪዎች ፕሮግራሙ በትምህርት ቤቱ ካለ በመደበኛው ሥርዓተ ትምህርቱ ፕሮግራም መሳተፍ ይችላሉ። ሆኖም ግን ትምህርት ቤቱ ያለው የጥንድ ቋንቋ ፕሮግራም ብቻ ከሆነ በመኖሪያ ቤቱ አቅራቢያ ወደሚገኘው በዚያ የክፍል ደረጃ ለመቀበል አቅም ባለው ት/ቤት የፕሮግርም ዝውውር ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።

የፕሮግራም ዝውውር ያገኙ ተማሪዎች ወንድምና እህት ተማሪዎች ወንድሞቻቸው በሚመሩበት ትምህርት ቤት እንዲገቡ ይፈቀዳል ምንም እንኳ የትምህርት ቤቱ የክፍል መጠን የሞላ ቢሆንም።

ከትምህርት ቤት ፕሮግራሙ ለሚገቡ ወይም ለሚወጡ ቤተሰቦች የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል።

የፕሮግራም ዝውውር ያገኙ ተማሪዎች በቀጣዪ የትምህርት አመት መጀመሪያ ላይ በመኖሪያ ዞናቸው ወደ አለው ትምህርት ቤት እንዲመለሱ መጠየቅ ይችላሉ። እነዚህ ጥያቄዎች ተቀባይነት የሚያገኙት በተጠየቀው የክፍል ደረጃ ክፍት ቦታ የሚኖር ከሆነ ነው። በትምህርት ዓመቱ የሚቀርቡ ማናቸውም ጥያቄዎች እንደየጥያቄው ሁኔታ አንድ በአንድ ይታያሉ።

### መዋእለ ህጻናት - 8 ትምህርት ቤቶች

*መዋእለ - 8 ትምህርት ቤት በቅድሚያ በትምህርት ቤት ዞኑ ለሚኖሩ ተማሪዎች ክፍት ይሆናል። ከዞኑ ውጭ ኖሪ ለሆኑ ተማሪዎች ዝውውር የሚቀበለው በዚያ የክፍል ደረጃ ክፍት ቦታ ካለው ብቻ ነው። በትምህርት ቤት ዞናቸው በተመደቡበት መዋእለ - 8 ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች መግባት ይችላሉ ።*

*መዋእለ - 8 ትምህርት ቤት የሚከታተሉ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ከስድስተኛ ክፍል ጀምሮ መውጣት ይችላሉ ሆኖም ከዚያ በፊት አይቻልም። በመዋእለ - 8 ትምህርት ቤቶች ያለው የመዋእለ - 5 ፕሮግራሞች በመደበኛ ት/ቤቶች ከሚሰጠው ፕሮግራም ጋር ተመሳሳይ ነው። ተማሪዎች የመካከለኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በዚያ ትምህርት ቤት እንዲቀጥሉ ይደረጋል እነርሱ በዞናቸው መደበኛ የመካከለኛ ድረጃ ት/ቤት ለመግባት ካልመረጡ በስተቀር።*

የፕሮግራም ዝውውር ያገኙ ተማሪዎች ወንድምና እህት ተማሪዎች ወንድሞቻቸው በሚመሩበት ትምህርት ቤት እንዲገቡ ይፈቀዳል ምንም እንኳ የትምህርት ቤቱ የክፍል መጠን የሞላ ቢሆንም።

ከትምህርት ቤት ፕሮግራሙ ለሚገቡ ወይም ለሚወጡ ቤተሰቦች የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል።

የፕሮግራም ዝውውር ያገኙ ተማሪዎች በቀጣዪ የትምህርት አመት መጀመሪያ ላይ በመኖሪያ አካባቢያቸው ወደ አለው ትምህርት ቤት እንዲመለሱ መጠየቅ ይችላሉ። እነዚህ ጥያቄዎች ተቀባይነት የሚያገኙት በተጠየቀው የክፍል ደረጃ ክፍት ቦታ የሚኖር ከሆነ ነው። በትምህርት ዓመቱ የሚቀርቡ ማናቸውም ጥያቄዎች እንደየጥያቄው ሁኔታ አንድ በአንድ ይመረመራሉ።

## የተሻሻለ የጊዜ ሰሌዳ (ካላንደር) ፕሮግራም

የተሻሻለ የጊዜ ሰሌዳ (ካላንደር) ፕሮግራም የሚከታተሉት የትምህርት ቀናት ቁጥር በመደበኛ ትምህርት ቤት ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው። ነገር ግን ሰላሳ ተጨማሪ የትምህርት ቀናት የመከታተል አማራጭ አላቸው። ተጨማሪዎቹ ቀናት በዓመቱ በመላ የተሰራጩ በመሆኑ በክፍለ ግዜዎች(ኢንተር ሲሽን) መሃል ባለው ጊዜ ተማሪዎች በተራዘመ የትምህርት ክፍለ ጊዜ የመሳተፍ እድል ይኖራቸዋል ።

የተሻሻለ የጊዜ ሰሌዳ (ካላንደር) ፕሮግራም ትምህርት ቤት በቅድሚያ እድል የሚሰጠው በትምህርት ቤት ዞኑ ኖሪ ለሆኑ ተማሪዎች ብቻ ነው። ከትምህርት ቤት ዞኑ ውጭ ያሉ ዝውውር የሚቀበለው በዚያ የክፍል ደረጃ ክፍት ቦታ ካለ ብቻ ነው።

በትምህርት ቤት ዞኑ ኖሪ የሆኑ የተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች የተሻሻለውን የጊዜ ሰሌዳ (ካላንደር) ፕሮግራም መከታተል የማይፈልጉ በተማሪው አቅራቢያው ወደአለ በዚያ የክፍል ደረጃ የመቀበል አቅም ባለው ትምህርት ቤት የፕሮግራም ዝውውር መጠየቅ ይችላሉ።

የፕሮግራም ዝውውር ያገኙ ተማሪዎች ወንድምና እህት ተማሪዎች ወንድሞቻቸው በሚመሩበት ትምህርት ቤት እንዲገቡ ይፈቀዳል ምንም እንኳ የትምህርት ቤቱ የክፍል መጠን የሞላ ቢሆንም።

ከትምህርት ቤት ፕሮግራሙ ለሚገቡ ወይም ለሚወጡ ቤተሰቦች የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል።

የፕሮግራም ዝውውር ያገኙ ተማሪዎች በቀጣዪ የትምህርት አመት መጀመሪያ ላይ በመኖሪያ አካባቢያቸው ወደ አለው ትምህርት ቤት እንዲመለሱ መጠየቅ ይችላሉ። እነዚህ ጥያቄዎች ተቀባይነት የሚያገኙት በተጠየቀው የክፍል ደረጃ ክፍት ቦታ የሚኖር ከሆነ ነው። በትምህርት ዓመቱ የሚቀርቡ ማናቸውም ጥያቄዎች እንደየጥያቄው ሁኔታ አንድ በአንድ ይመረመራሉ።

## III. አስተዳደራዊ ዝውውር

የተማሪውን ልዮ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ወላጆች ለልጃቸው(ጆቻቸው) አስተዳደራዊ ዝውውር መጠየቅ ይቻላሉ። አስተዳደራዊ ዝውውር ማለት አንድ ተማሪ በደህንነት፣ ጤና ወይም ጊዚያዊ ወይም በትምህርት ዓመቱ መሃል የመኖሪያ ቤት መቀየር ምክንያት በወላጅ/አሳዳጊ ጥያቄ እና በአስተዳደር ሃላፊ በተሰጠ አስተዳደራዊ ፍቃድ ተማሪው ተጠቃሚ ለማድረግ የትምህርት ቤት አካባቢ እንዲቀየር ከአንድ ት/ቤት ወደሌላ እንዲዛወር ማድረግ ነው ። አስተዳደራዊ ዝውውር ፈቃድ የሚሰጠው በሱፐር ኢንቴንደንቱ ወይም ስልጣን በተሰጠው ተወካይ ነው።

### በትምህርት ቤት ዲቭዝኑ የውስጥ ዝውውር

ኤሲፒኤስ ትምህርት ቤት የሚከታተል ተማሪ እና ቤተሰብ የትምህርት ዘመኑ ከተጀመረ በሆላ ወደሌላ የኤሲፒኤስ የትምህርት ቤት ዞን ከቀየሩ በአሁን እርሱ/እርሷ ባበለት/ባለችበት ትምህርት ቤት ለዚያ የትምህርት ዓመት በአስተዳደራዊ ዝውውር ፈቃድ ብቻ የመቆየት ምርጫ ይኖረቸዋል። ተማሪው በዚያ ትምህርት ቤት ለመቆየት ከመረጠ የትራንስፖርት አገልግሎት አያገኝም።

### ወደ ሌላ የትምህርት ዲቪዝን መቀየር

የአምስተኛ ክፍል ተማሪ የኤሲፒኤስ ትምህርት ቤት የሚከታተል እና በአራተኛው ኮርተር ወቅት ቤተሰቡ ወደ ሌላ የትምህርት ዲቪዝን የቀየረ የአስተዳደር ፍቃድ በማግኘት አሁን በሚከታተልበት ትምህርት ቤት በትምህርት ዘመኑ የመጨረስ ምርጫ ያገኛል ። በተጨማሪ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪ የኤሲፒኤስ ትምህርት ቤት እና ከሁለተኛው ኮርተር በኋላ ቤተሰቡ ወደ ሌላ የትምህርት ዲቪዝን የቀየሩ አሁን እርሱ/እርሷ በሚከታተሉበት ትምህርት ቤት የትምህርት ዘመኑን የመጨረስ ምርጫ ያገኛሉ ። ይህ በተለይ የሚሰጥ ፈቃድ በተማሪው ጥሩ ባህሪ ማሳየት፣ በትምህርት መከታተል፣ እና የአካዳሚ ሁኔታ ላይ ይመሰረታል። የትራንስፖርት አገልግሎት አይሰጥም።

በወላጅ/አሳዳጊ ጠየቂነት ለሚደረግ አስተዳደራዊ ዝውውር የትራንስፖርት አገልግሎት አይሰጥም። በጣም በተለየ ሁኔታ በሱፐር ኢንቴንደንት ወይም በተወካዩ በደንብ ተመርምሮ የትራንስፖርት አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል።

እንደሌሎቹ ዝውውሮች ሁሉ ሁሉም የዝውውር ጥያቄ ከመቅረቡ በፊት ተማሪዎች በመጀመሪያ በዞናቸው ባሉ ትምህርት ቤቶች መመዝገብ አለባቸው ።

አስተዳደራዊ ዝውውር ያላቸው ተማሪዎች በመጪው የትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ በዞናቸው ባሉ ትምህርት ቤቶች ለመመለስ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ ። እነዚህ ጥያቄዎች ተቀባይነት የሚያገኙት በተጠየቀው የክፍል ደረጃ

ለመቀበል አቅም ካለ ነው። በትምህርት ዓመቱ የሚቀርቡ ማናቸውም ጥያቄዎች እንደየጥያቄው ሁኔታ አንድ በአንድ ይመረመራሉ።

**<u>የከተማ አቀፍ ፕሮግራም የአካል ጉዳት ላላቸው ተማሪዎች</u>**

በአይ.ኢ.ፒ(IEP) ቡድን ምደባ መሰረት በከተማአቀፍ ልዩ የትምህርት ፕሮግራም የሚመደቡ ተማሪዎችን ይህ ፖሊሲ አይመለከትም። እነዚህም ፕሮግራሞች የስሜት ጉዳት(ኢሞሽናል ዲሴብሊቲ-ED)፣ የአእምሮ ጉዳት (ኢንተሌክችዋል ዲሴብሊቲ- ID)፣ በርካታ ጉዳት(መልቲፐል ዲሴብሊቲ- MD)፣እና ኦቲዝም ያላቸው ተማሪዎች ፕሮግራሞች እና ቅድመ መደበኛ ትምህርት ልዮ ትምህርት (ECSE)ያጠቃልላል።

የፀደቀው፤ ዲሴምበር 5፣ 1996
የተሻሻለው፤ ጁን 15፣ 2004
የተሻሻለው፣ ጁላይ 1 ፣ 2005
የተሻሻለው፣ ማርች 11 ፣ 2010
የተሻሻለው፣ ኤፕሪል 25፣ 2013
የተሻሻለው፣ ሜይ 19፣ 2016

የህግ ማጣቀሻ፤ የቨርጅኒያ ሕግ፤ 1950 እንደተሻሻለው §§ 22.1-78, 22.1-79

| | | |
|---|---|---|
| የቃላት ማስታወሻ ፤ | IHB | የክፍል ብዛት መጠን |
| | IHB-R | ከክፍል ብዛት ጋር የተያያዙ ደንቦች |
| | JCA | የወንጀል ተጠቂ የሆነ ተማሪ ዝውውር |
| | JCB | በተከታታይ አደገኛ የሆነ ት/ቤቶች የተማሪ ዝውውር |
| | JC-R/JCD-R | የኤሲፒኤስ ተማሪ ምደባ አማራጮች የሚመለከት ደንቦች |
| | JCE | የዞን መልሶ ክፍፍል አፈፃፀም |
| | JCE-R | የዞን መልሶ ክፍፍል አፈፃፀም ደንቦች |
| | JED | የተማሪ መቅረት/ፈቃድ/ ስንብት |